Monthly Newsletter Vol 17 No. 3

PRINTED BY
International & Public Relations Directorate

NOV
2020

# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

# Ethiopian Civil Service University



## የኢሲሰዩ

## የተማሪዎች ቅበላ ቅድመ ዝግጅት በተመለከተ ግምገማ ተካሄደ



“አካል ጉዳተኝነት ማለት በአካል እና በአዕምሮ ላይ የሚደርስ እክል ማለት ነው።”



## Woliso Training and Consultancy Service Holds Induction Training

## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## እሴቶቻችን

ተገልጋይ ተኮር
ቁርጠኝነት
ሁሌም መማር
ብዝሀነት መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
አሳታፊነት
ተባብሮ መስራት

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, Transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education,Training, Consultancy, Research and Community Services.

## Our Values

Customer Focus
Commitment
Continuous Learning
Welcoming Diversity
Attention to the Disadvantaged
Participation
Collaboration

# Ethiopian Civil Service University

## Content


1 የኢሲሰዩ የተማሪዎች ቅበላ ቅድመ ዝግጅት በተመለከተ ግምገማ ተካሄደ

3 TCS Cascades Annual Plan

4 Gender and HIV/AIDS Prevention and Control Directorate Gives Training

5 Woliso Training and Consultancy Service Holds Induction Training

6 የሥርዓተ-ፆታ እና ኤች.አይ.ቪ / ኤድስ መከላከያ እና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

8 የፋይናንስ አጠቃቀም በፋይናንስ ምንጭ ከ ሃምሌ 1/2011ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2012



**Editor In -Chife**
Tariku Ayano

**Editors**
Anteneh Demisse
Meley Tekeste

**Photos**
Ibsa Bekele
Dereje Tesfaye

**ግራፊክስ እና LAYOUT DESIGN**
Dereje Tesfaye


# የዝግጅት ክፍሉ መልእክት

የኮቪድ 19 ቫይረስ ወደ ሀገራችን መግባቱ ከተረጋገጠበት ጊዜ አንስቶ እንደ ሀገርም ሆነ በዩኒቨርሲቲያችን ደረጃ ማህበረሰቡን ከወረርሺኙ ለመታደግ በርካታ የጥንቃቄ ስራዎች ሲከናወን መቆየቱ የሚታወቅ ነው፡፡ ሆኖም የወረርሽኙ ስጋት እንደታሰበው በአጭር ጊዜ የሚወገድ አለመሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ቀደም ሲል ተቋርጦ የነበረው መደበኛ ስራና እንቅስቃሴ ወደነበረበት ሁኔታ በበመለስ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ መዘናጋትን እያስከተለ መሆኑ በገሀድ እየታየ ነው፡፡ በመሆኑም መላው የዩኒቨርሲቲያችን ሰራተኞች የኮረና ቫይረስን አደገኛነት በመገንዘብ፤ እራሳቸውንና ማህበረሰቡን ከወረርሽኙ ለመከላከል በሚያደርጉት ጥንቃቄ ላይ ምንም አይነት መዘናጋት እንዳይኖር፤ የመማር ማስተማር ስራውም በመደነኛነት በሚጀመርበት ወቅት ለተማሪዎቻችንም አርአያ በመሆን የመከላከል እንቅስቃሴውን በተግባር እንዲደግፉ የጠበቀ መልዕክታችንን ለማስተላለፍ እንወዳለን፡፡

ውድ አንባቢያን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ ህንጻ ቁጥር5 ቢሮ ቁጥር 210 ድረስ በአካል በመምጣት ወይም በኢሜል pr.ecsu@gmail.com አድራሻችን በመላክ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡በተጨማሪ የኤሌክትሮኒክስ ወርሃዊ ህትመታችንን በ ድህረገጻችን (www.ecsu.edu.et) GALLERY (Megazine and Newsletter) በሚለዉ ስር ታገኛላቹ ፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# የኢሲሰዩ የተማሪዎች ቅበላ ቅድመ ዝግጅት በተመለከተ ግምገማ ተካሄደ

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ 2013 የት/ዘመን የተማሪዎች ቅበላ ቅድመ ዝግጅት በተመለከተ ከሣይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በመጡ የሥራ ኃላፊዎች አጠቃላይ ግምገማ ጥቅምት 20/ 2013 ተደረገ፡፡



የኢሲሰዩ ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ለገምጋሚ አባላቱ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግራቸዉን ካስተላለፉ በኋላ የኢ.ሲ.ሰ.ዩ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን በመቋቋም የተቋረጠውን ትምህርትና ስልጠና ለማስጀመር በሚቻልበት ሁኔታ የተለያዩ ስራዎች ሲሰራ ቆይቷል ፡፡ በዚህም ተማሪዎችን ደረጃ በደረጃ መልሶ ለመቀበል የሚያስችሉ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች እንዲሁም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ተለይተው የስራና አፈፃፀም መመሪያ ተሰጥቶባቸዉ ለቅበላዉ የተለያዩ ዝግጅቶችም ተደርገዋል ብለዋል ፡፡



ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተወክለዉ የመጡት አባላትም በዋናነት ትምህርትና ስልጠናውን ለማስጀመር ተቋሙ ያሉበትን ደረጃ በተለይ ኮቪድ 19 ከመከላከል አንጻር በተጨባጭ እየሰሩ ያሉትን ስራዎችና የኮቪድ ፕሮቶኮልን ከመተግበር አንጻር የገመገሙ ሲሆን የዩንቨርስቲዉን አጠቃላይ የተማሪዎች ቅበላ ዝግጅት በተመለከተ የተለያዩ የስራ ክፍሎችን ጎብኝተዋል፡፡

ተቋማችን የለይቶ ማቆያ በመሆን አገልግሎት ስንሰጥ መቆየታችን ብዙ ተሞክሮ እንድንወስድ አድርጎናል ለዚህም ቅድመ ዝግጅታችንን ቀድመን አከናዉነናል ማለት ይቻላል በማለት በተለይ በመጀመሪያ የኮቪድ ወቅት በሰራተኛዉ ዘንድ የነበሩ ፍርሀቶች በሙሉ አሁን እንደተቋም በተሰሩ የግንዛቤ ስራዎች ቀንሶአል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቻችንን ለመቀበል ብዙም አንቸገርም ፡፡ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ እራሳችንን እየተከላከልን ሰላማዊ እና ምቹ የመማር ማስተማር ሂደትን በመፍጠር ተማሪዎቻችንን ለመቀበል ዝግጅታችንን ጨርሰናል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በዝግጅት ምዕራፍ የተሰሩ ስራዎችን ለገምጋሚዎቹ አብራርተዋል፡፡



**ፕ/ ር ፍቅሬ ደሳለኝ**
*የኢሲሰዩ ፕሬዚዳንት*

በጉብኝቱም ማጠናቀቅያ ላይ ሲገልጹ የተማሪዎች መመገብያ አዳራሽ፣ ቤተመጽሀፍትና ዶርሚተሪዎች አጠቃላይ ኮቪድ ለመከላከል በሣይንስና ከፍተኛ ትምህርትና ጤና ሚኒስቴር የተቀመጡት ፕሮቶኮሎች እንደሚያሟሉ በተለይ ተቋሙ በተጨባጭ እየሰራቸዉ ያሉ ስራዎች ለሌላም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንደ ሞዴል የሚታይ መሆኑን በሰጡት አስተያየት በመግለጽ የተቀሩትን የዝግጅት ሥራዎች በማጠናቀቅ ተማሪዎችን በታቀደው መርሀ ግብር የመቀበል ቁመና ላይ መሁኑን ገልጸዋል ።በተጨማሪም ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎች መመሪያዎችን በጥብቅ ዲሲፒልን እንዲፈፅሙ ክትትል አስፈላጊ መሆኑን አበክረዉ አሳስበዋል።

























# TCS Cascades Annual Plan

Ethiopian Civil Service University Training and Consultancy Service cascaded the 2020/21 academic year annual plan to the centers and directorates in the wing. Dr. Waqgari Negari Vice president for Training and Consultancy Service signed the agreement with the respective centers and directorates directors to implement the cascaded plan on December 4, 2020 at Hidasse Hall.



**Dr. Waqgari Negari**
*Vice President, Training and Consultancy services*

On the signing program, Dr. Waqgari Negari called up on the directors to begin their work with a new spirit and motivations. "This agreement should not be made in the usual and traditional way, but should be signed by upgrading and integrating ourselves with the situation that we face. We have learned a major lesson from the accidental occurrence of the COVID 19 that happened last year. By this, we need to come up with new ideas while an unexpected situation happens and think how we can manage, and learned from them," he said.

Dr. Waqgari also noted that planning alone is not enough and it needs to be implemented. In order to implement the plan properly, we need psychological preparation to work hard and follow up our activities. Besides, handling of issues related to resource, human power and time must be under consideration, he underscored.

On the program, the best performers of the year 2019/2020 from each centers and directorates have been recognized for their achievement.











# Gender and HIV/AIDS Prevention and Control Directorate Gives Training

Ethiopian Civil Service University Gender and HIV/AIDS Prevention and Control Directorate gave awareness raising training to ECSU staff on October 28, 2020, at Hidasse Hall. The main purpose of the training was to give the university community a deep sight on gender and disability related issues and the importance of mainstreaming and affirmative action.



**Ato Zinabe Tadesse**
*ECSU Gender and HIV/AIDS Prevention and Control Directorate Director*

On the training, Ato ZinabeTadesse, ECSU Gender and HIV/AIDS Prevention and Control Directorate Director, said gender and disability affair is a matter that requires the community's attention and working together on filling the gap on knowledge and attitude towards the issue. In addition policies and laws must consider persons with disabilities when they are designed and ratified.





He also underscored the importance of mainstreaming them by focusing on capacity building from the community's core objectives and providing affirmative action focusing on empowering and supporting women and people with disabilities and need to be supported by budgeting in the future. Besides crosscutting issues need to be includeed include in higher education curriculums.





# CPLHR Establishes a Forum

Ethiopian Civil Service University Center for Policy, Leadership and Human Resource established "Competency Teams Forum" on October 23, 2020 at ECSU Training Hall.



**Ato Abebe Tegegn**
*Director for Center for Policy, Leadership and Human Resource Training and Consultancy*

According to Ato Abebe Tegegn, Director for Center for Policy, Leadership and Human Resource Training and Consultancy, the forum is established to facilitate consistent implementations of the six projects that are being implemented by the agreement signed between Ethiopian Civil Service University and Ethiopian Civil Service Commission on May 11, 2020 and it is believed to serve as linkage for smooth implementation of these projects being implemented by different actors. These projects include; Provision of training on the preparation of a human resource qualification framework, the preparation of document on basic human resource certification framework, preparation of a human resource technical certification framework, the establishment of



a competency assessment center, establishment of information and assessment system supported by information communication technology and provision of training for civil service institutions on preparation of capacity building module.



He also noted that these projects have a total budget of 11105407.20 Birr and the forum consists of four groups and fifteen members led by Center for Policy, Leadership and Human Resource.



# Woliso Training and Consultancy Service Holds Induction Training

Ethiopian Civil Service University, Woliso Training and Consultancy Service Center held induction training program for staff members of the center on October 18, 2020 at Woliso Training Center. The training was given by Ato Negussie Deriba, Director for Wolliso Training Center and 28 staff members attended the training.



**Ato Negussie Deriba**
*Director for Wolliso Training Center*



On the training Ato Negussie explained and gave extended explanation on government policies, strategies, laws and regulations based on the Public Service Proclamation. Besides, he explained the workers' rights and obligations and workers' discipline and disciplinary action that will be taken in the occurrence of disciplinary problems.

He also gave a detail explanation for the questions raised by the trainees.





# ቆይታ

## ኢ.ሲ.ሰ.ዩ የሥርዓተ-ፆታ እና ኤች.አይ.ቪ / ኤድስ መከላከያ እና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር

***የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሥርዓተ-ፆታ እና ኤች.አይ.ቪ / ኤድስ መከላከያ እና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ማብቃትን መሰረት ያደረጉ ስራዎችን በመስራት ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንንም ስራ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ለዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች እና ተማሪዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት የግንዛቤ ማስጨበጫና የሚታዩ ክፍተቶችን የመሙላት ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ እኛም ክፍሉ በዚህ አመት ካለው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አቀባበል ጋር በተያያዘ እየተሰሩ ያሉት ስራዎችን ለመቃኘት ከክፍሉ ዳይሬክተር ከአቶ ዝናቤ ታደሰ ጋር ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበናል ፡፡ መልካም ቆይታ፡፡***

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- በመጀመሪያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ በመሆንዎ ከልብ እናመሰግናለን፡፡***

***አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-*** እኔም አመሰግናለው፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- አካል ጉዳተኝነት ሲባል ምን ማለት ነው?***

***አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-*** አካል ጉዳተኝነት ማለት በአካል እና በአዕምሮ ላይ የሚደርስ እክል ማለት ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን እንዳፀደቁት የአካል ጉዳኝነት በተለያዩ ምክንያቶች የሚደርስና በአካል እና አዕምሮ ላይ የሚደርሱ እና ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ እክሎች ሲያጋጥሙ የአካል ጉዳተኛነት ተከሰተ እንላለን፡፡ በዚህም ትንታኔ ላይ 174 የአለም አገራት ተስማምተውበት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ላይ ስለአካል ጉዳተኝነት ምንነት እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- ማህበረሰቡ አካል ጉዳተኝነትን በምን አይነት መንገድ ይረዳዋል?***

***አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-***ማህበረሰቡ አካል ጉዳተኝነትን በአራት አይነት መንገድ ይመለከተዋል፡፡ የመጀመሪያው ምድብ በጎ አድራጊ በመባል የሚታወቀው ሲሆን ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ ማንኛቸውም ነገሮች፤ ድጋፍም ይሁን እርዳታ ከለጋስነት አንፃር እንጂ የአካል ጉዳተኛውን ግለሰብ መብት በማወቅ የሚያደርጉት አይደለም፡፡ ሁለተኛውና ሜዲካል ሞዴል በመባል የሚታወቀው ደግሞ አካል ጉዳተኞቹ ያለባቸውን ችግሮች ለይቶ በማወቅና መፍትሄዎችን መፍጠርና ተግባራዊ በማድረግ ብቁ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚሰሩ ናቸው፡፡ እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎችም በአብዛኛው የጤና ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ሶስተኞቹ ማህበራዊ ሞዴል ይባላሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ "አካል ጉዳተኝነት እንደማንኛውም ዜጋ ማንኛውንም ተግባር መተግበር የሚሉ ናቸው፡፡ ችግሩን የፈጠርነው እኛው እራሳችን ባልሆነ አስተሳሰብ ነው ፡፡ አስፈላጊውን ነገር ማሟላት ከተቻለ በማንኛውም የስራ መስክ ላይ ተደራሽና ውጤታማ ይሆናሉ፡፡" ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡ አራተኛው የማህበረሰብ ክፍል ሰብዓዊ መብት ሞዴል በመባል የሚታወቁ ሲሆን በአለም አቀፍ ደረጃ አካል ጉዳተኝነት በማንኛውም እንቅስቃሴ ላይ ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር እኩል መብት አላቸው ብለው የሚያምኑ ሲሆኑ በዚህም አለም አቀፍ ኮንቬንሽን ላይ ወደ 52 አንቀፆች ያዘጋጁ ናቸው፡፡ እነዚህ አንቀጾችም አካል ጉዳተኛ ማህበረሰቦችን በማንኛውም ሁኔታ ላይ አካታች እና ተደራሽ ለማድረግ ታልመው የተዘጋጁ አንቀጾች ናቸው፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- በዳይሬክቶሬቱ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አመለካከት ለመረዳትና ለመለወጥ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ምን ምን ናቸው?***

**አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-** የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ የምንለው የዩኒቨርሲቲውን ሰራተኞች እና ተማሪዎችን ሲሆን አለም አቀፍ ኮንቬንሽን ባፀደቃቸው ህጎች ለመመራት እና የአካል ጉዳኞችን መብት እንዲያውቁ ለማድረግ የተለያዩ ስልጠናዎች የሚሰጡ ሲሆን በቋሚነትም በዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ የሬዲዮ ጣቢያ ላይ ተከታታይ የሆነ ፕሮግራም አለ፡፡ በዚህ ፕሮግራም ላይ የማህበረሰቡን አመለካከት ለመቀየር ከፍተኛ ስራ እየሰራን እንገኛለን፤ የተሻለ ለውጦችንም ተመልክተናል፡፡ ለውጦችንም በተደጋሚ በሚደረጉ ስልጠናዎች ላይ የምንከታተልና ከፍተኛ ባይባልም በቂ የሚባሉ ግንዛቤዎችን ለማስቀመጥ ችለናል፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- በዩኒቨርሲቲው ምን ያህል አካል ጉዳተኛ ሰራተኞች አሉ?***

**አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-** በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ 9 (ዘጠኝ) አካል ጉዳተኛ ሰራተኞች አሉን፡፡ እነሱን የመለየት ስራው የሚሰራው በአብዛኛው አካል ጉዳተኞቹ በራሳቸው መጥተው ያለባቸውን የአካል ጉዳት አይነት ገልጸው ድጋፍ ወይም እንዲመቻቹላቸው የሚፈልጓቸውን ነገሮች መጥተው እንዲነግሩን በምናደርገው ስራ ነው ፡፡ ከዚያ ውጪ እኛ በራሳችን አንተ የዚህ አይነት ድጋፍ ያስፈልግሀል ብለን አንላቸውም፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- አዳዲስና ነባር ተማሪዎች በቅርቡ ትምህርታቸውን ይጀምራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ አንጻር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለማሟላት ያስችላችሁ ዘንድ ምን ያህል አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንዳሉ የለያችሁበት ሁኔታ ካለ ቢገልጹልን?***

**አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-** አዲስ እና ነባር አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አሉን፡፡ ነባር 46 አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ያሉን ሲሆን 36 (27 ወንድ እና 9 ሴት) መደበኛ እና 10 (9 ወንድ እና 1 ሴት) የክረምት ተማሪዎች አሉን፡፡ እነሱም ማየት የተሳናቸው (ሙሉ ለሙሉ እና በከፊል)፣ የመማር እክል ያለባቸው፣ የአከርካሪ መጉበጥ፣ የእንቅስቃሴ እክል እና ዊለቸር ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በ2013 መርሀ ግብር ላይ ካለው ወቅታዊ የኮሮና በሽታ ምክንያት ምን ያህል አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንዳሉን ለማወቅ አልቻልንም፡፡ ከዚህ ቀደም ከምዝገባ በኋላ የስብሰባ አዳራሾች ላይ በመጥራት ቁጥሩንም ሆነ ያሉትን ሁኔታዎች የምናውቅ የነበረ ሲሆን በዚህ አመት ግን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በየዶርሙ እየገባን ያሉትን ነገሮች የምናጣራ ይሆናል፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- ተማሪዎቹን ለመቀበል ምን አይነት ቅድመ ዝግጅት እ የተደረገ ነው?***



***አቶ ዝናቤ ታደሰ***
*የሥርዓተ-ፆታ እና ኤች.አይ.ቪ / ኤድስ መከላከያ እና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር*

**አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-** የሚመጡት ተማሪዎቻችን እንደአለባቸው የጉዳት ዓይነት ሊመቻቸው በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው እንዲማሩ ለማድረግ በጊቢው ውስጥ በመገንባት ላይ ያሉ ህንፃዎች አሉ፡፡ እነዚህ ህንፃዎችም በመመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀፅ 33 መሰረት እየተገነቡ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በጊቢው መንገዶች ላይ የተለያዩ ጠቋሚ ምልክቶችን አድርገናል፡፡ለጊቢው ሰራተኞችም ኮንቬንሽኑን መሰረት ያደረገ እና አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ማድረግ በሚል ርዕስ ስልጠና ሰጥተናል፡፡ ተማሪዎቹም በሚመጡበት ወቅት አገልግሎቶችን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ እና የአጠናን ስልትን በተመለከተ ስልጠና እንሰጣለን፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- በተቋሙ የሚገኙ ሰራተኞች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሰጡት አገልግሎት ቀልጣፋ ለማድረግ በተለየ ሁኔታ የሚሰሩ ስራዎች አሉ?***

**አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-** ሰራተኞች በስልጠናው ወቅት ኃላፊነት እንዳለባቸዉ ለማስረዳት ተሞክሯል፡፡



በተጨማሪም እንደ ግዴታም የሚወሰዱ ነገሮች አሉ፡፡ በራሱ ተነሳሽነት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ብቁ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ የሆነ የትብብር ስራ እንዲሰሩ በስልጠናም ወቅት የተገለጸ ሲሆን ተግባራዊ እንደሚሆንም እምነታችን የጸና ነው፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- ከአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ጋር በተያያዘ በመማር ማስተማሩ ላይ እየገጠሙ ያሉት ችግሮች ምንድናቸው?***

***አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-*** አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ባለፉባቸው የትምህርት አሰጣጥ ላይ አስፈላጊና መሰረታዊ ነገሮች እየተሟሉላቸው ባለመቆየታቸው እና በቂ የሆነ ልምድ ባለመያዛቸው ምክንያት ከሁኔታዎች ጋር በቶሎ ለመላመድ ሲቸገሩ ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ ማየት የተሳናቸው ተማሪዎች JAWS የሚባል ሶፍት ዌር አለ፡፡ እሱን ሶፍት ዌር ለመጠቀም የኮምፒውተር አጠቃቀም ማወቅን ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ልምዱ ስለሌላቸው እሱን እንዲለምዱ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ ችግር አለ፡፡ ሌላው ወደ መማሪያ ክፍል የድምፅ መቅጃዎችን ይዘው በሚገቡበት ጊዜ ትንሽ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የመማሪያ አጋዥ መሳሪያዎች ያስፈልጋሉ፡፡ መሳሪያዎቹን ማሟላት ደግሞ ከአካዳሚክ ክፍሉ የሚጠበቅ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች እቅድ ሳይያዝ ቀርቶ መሳሪያዎቹ ሳይገዙ ይቀራሉ፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ መሳሪያዎቹን ባለማግኘታቸው ምክንያት አንድና ከዚያም በላይ የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች ያመልጧቸዋል፡፡ በተጨማሪም የዲፓርትመንት መረጣ ላይም ችግሮች አሉ፡፡ ተማሪዎቹ ለነሱ አመቺ ያልሆነ ትምህርቶችን ይመርጣሉ፡፡ እነዚህን ችግሮችም በጊዜው ለማግባባትና ለመፍታት ጥረት እናደርጋለን፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- በቀጣይ እንደክፍል ሊሰሩ የታቀዱ እንዲሁም የተቋሙ ማህበረሰብ ቢያደርጓቸው የሚሉት ነገር ካለ፤ አያይዘውም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ?***

***አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-*** ከዚህ በፊትም አሁንም እያደረግናቸው ያለናቸው እንቅስቃሴዎች አሉ፡፡ እነርሱ እንዳሉ የሚቀጥሉ ሲሆን ስልጠናዎቹም በደንብ ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናሉ፡፡ ሌላው ክፍሉ በጀት ተበጅቶለት በራሱ መንቀሳቀስ ቢችል የተሻለ ይሆናል ብለን እናምናለን፡፡ ለዚህም ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመወያየት አስፈላጊውን ግብዓት ግዢ እንዲካሄድ የግዥ ፍላጎት ጥያቄ አቅርበናል፡፡ እስካሁን ለአካል ጉዳተኞቹን መርጃ መሳሪያዎች ግዥ ሲደረግና የተገዙትም በብልሽት ምክንያት መጠገን ሲያስፈልጋቸው በአጋርነት የሚሰሩ ተቋሞች አሉን፡፡ እነሱን በዩኒቨርሲው ስም ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ማህበረሰቡም ለአካል ጉዳተኞች እርዳታ ሳይሆን አቅማቸውን እንዲያጎለብቱና ብቃታቸውን እንዲያሳዩ በሁሉም መስክ አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርጉ መልዕክቴን ማስተላለፍ እወዳለሁ ፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- ለቃለ ምልልሱ ስለተባበሩን እናመሰግናለን፡፡***

***አቶ ዝናቤ ታደሰ፡-*** እኔም አመሰግናለዉ፡፡

# የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ

በኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣውን የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 668/200 ለማስፈፀም የተሻሻለው የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 13/2013ዓ.ም በሁሉም የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ተግባራዊ እንዲሆን የፌደራል የስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አሳውቆናል፡፡

ምዝገባው በመንግስት አሰራር ወስጥ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ያለው አሠራር ለማስፈን፣ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እና የመንግስት የሥራ ኃላፊነት እና የግል ጥቅም ሳይቀላቀሉ በየራሳቸው መንገድ የሚመሩበትን ሥርዓት በመዘርጋት ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት ለማስወገድ ዓላማ አድጎ የተዘጋጀ ሲሆን በአራት አይነት አመዘጋገብ የሚከናወን ነው፡፡

1. የመጀመሪያ ምዝገባ፡- ማንኛውም ተሿሚ፤ተመራጭ ወይም የመንግስት ሰራተኛ እንደ ተመደበ የገቢ ምንጩን የሚያስመዘግብበት ምዝገባ ነው፡፡

2. የእድሳት ምዝገባ ፡- አንድ ሀብት አስመዝጋቢ ሀብቱን ካስመዘገበ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ የሚያደርግ ምዝገባ ነው፡፡

3. አገልግሎት የማቋረጥ ምዝገባ፡- ማንኛውም ሀብት አስመዝጋቢ ሀብቱን ካስመዘገበ 6 ወርና ከዚያ በላይ ሲሰራ ቆይቶ በማንኛውም ምክንያት መስሪያ ቤቱን ለቆ ሲወጣ የሚያደርግ ምዝገባ ነው፡፡

4. አገልግሎት ካቋረጡ ከ2 ዓመት በኃላ የሚደረግ ምዝገባ ፡- አንድ በጡረታ የተሰናበተ ወይም ሙሉ በሙሉ ከመንግስት ስራ የተሰናበተ ሀብት አስመዝጋቢ አገልግሎቱን ካቋረጠ ከ2 ዓመት በኃላ የሚያደርግ ምዝገባ ነው፡፡

## ሃብት አለማስመዝገብ ምን ምን ቅጣቶችን ያስከትላል?

በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 13/2013 ዓ.ም

▪በመደበኛ የማስመዝገቢያ ጊዜ ያላስመዘገበ ሰው ለፌደራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ብር 1,000.00 ከፍሎ በ30 ቀናት ውስጥ በኮሚሽኑ በአካል በመሄድ የሚያስመዘግብ ይሆናል፡፡ ሙሉ በሙሉ መስመዝገብ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው

▪በወንጀል ሕግ አንቀጽ 419/2 ድንጋጌ አፈጻጸም ያፈራው ሀብት ሁሉ ምንጩ እንዳልታወቀ ንብረት ሆኖ በሕግ ሊያስጠይቀው ይችላል፣

▪ማስረዳት ካልቻለ ንብረቱ ይወረሳል፣ እስከ 5 አመት በሚደርስ እስራትም ሊቀጣ ይችላል፤

▪እንደ መ/ቤቱ አሰራር እና ውስጠ-ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወሰድበት ይችላል፣

# የኢሲሰዩ ፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት ምንጭ ከሃምሌ 1/2011 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2012

| | ከግምጃ ቤት | | | ከውስጥ ገቢ | | | አጠቃላይ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈቀደ/የተስተካከለ | ወጪ የተደረገ | ወጪ የተደረገ % | የተፈቀደ | ወጪ የተደረገ | ወጪ የተደረገ % | አጠቃላይ የተፈቀደ በጀት | በአጠቃላይ ወጪ የተደረገ | ልዩነት | ወጪ የተደረገ% |
| የበጀት አርዕስት | 255,867,419.03 | 225,043,313.01 | 87.95 | 38,037,894.67 | 37,472,933.25 | 98.51 | 293,611,490.28 | 262,516,246.26 | 31,095,244.02 | 89.41 |
| 6111 | 82,062,847.52 | 81,805,181.34 | 99.69 | - | | | 82,062,847.52 | 81,805,181.34 | 257,666.18 | 99.69 |
| 6113 | 17,272.73 | | - | | | | 17,272.73 | - | 17,272.73 | - |
| 6114 | 1,770,000.00 | 1,725,437.46 | 97.48 | 1,826,128.00 | 1,754,497.28 | 96.08 | 3,596,128.00 | 3,479,934.74 | 116,193.26 | 96.77 |
| 6116 | 11,118,005.38 | 10,280,353.32 | 92.47 | 27,619,932.50 | 27,520,485.37 | 99.64 | 38,737,937.88 | 37,800,838.69 | 937,099.19 | 97.58 |
| 6121 | 4,518,000.00 | 3,866,894.67 | 85.59 | 1,074,300.00 | 1,048,325.33 | 97.58 | 5,592,300.00 | 4,915,220.00 | 677,080.00 | 87.89 |
| 6131 | 8,820,100.00 | 8,798,067.66 | 99.75 | | | | 8,820,100.00 | 8,798,067.66 | 22,032.34 | 99.75 |
| 6211 | 5,965,900.00 | 3,192,899.81 | 53.52 | | | | 5,965,900.00 | 3,192,899.81 | 2,773,000.19 | 53.52 |
| 6212 | 5,059,300.00 | 4,220,455.69 | 83.42 | 164,324.97 | 164,324.97 | 100.00 | 5,223,624.97 | 4,384,780.66 | 838,844.31 | 83.94 |
| 6213 | 1,807,175.00 | 1,416,782.48 | 78.40 | - | | | 1,807,175.00 | 1,416,782.48 | 390,392.52 | 78.40 |
| 6214 | 600,400.00 | 441,786.37 | 73.58 | | | | 600,400.00 | 441,786.37 | 158,613.63 | 73.58 |
| 6215 | 4,462,857.18 | 4,390,573.23 | 98.38 | | | | 4,462,857.18 | 4,390,573.23 | 72,283.95 | 98.38 |
| 6216 | 27,000,000.00 | 25,375,196.64 | 93.98 | 3,678,991.49 | 3,374,282.62 | 91.72 | 30,678,991.49 | 28,749,479.26 | 1,929,512.23 | 93.71 |
| 6217 | 2,329,526.75 | 1,999,110.53 | 85.82 | | | | 2,329,526.75 | 1,999,110.53 | 330,416.22 | 85.82 |
| 6218 | 7,338,499.50 | 7,223,156.19 | 98.43 | 1,302,376.01 | 1,277,976.01 | 98.13 | 8,640,875.51 | 8,501,132.20 | 139,743.31 | 98.38 |
| 6219 | 1,952,150.62 | 1,661,433.75 | 85.11 | | | | 1,952,150.62 | 1,661,433.75 | 290,716.87 | 85.11 |
| 6223 | 17,825,135.59 | 15,988,183.05 | 89.69 | 70,000.00 | 50,000.00 | 71.43 | 17,895,135.59 | 16,038,183.05 | 1,856,952.54 | 89.62 |
| 6231 | 421,171.41 | 300,098.10 | 71.25 | - | | | 421,171.41 | 300,098.10 | 121,073.31 | 71.25 |
| 6232 | 1,486,904.74 | 645,219.00 | 43.39 | - | | | 1,486,904.74 | 645,219.00 | 841,685.74 | 43.39 |
| 6233 | 1,590,825.55 | 1,289,239.85 | 81.04 | 600.00 | 600.00 | 100.00 | 1,591,425.55 | 1,289,839.85 | 301,585.70 | 81.05 |
| 6241 | 2,936,000.00 | 1,797,969.54 | 61.24 | | | | 2,936,000.00 | 1,797,969.54 | 1,138,030.46 | 61.24 |
| 6243 | 7,734,565.13 | 5,883,209.54 | 76.06 | - | | | 7,734,565.13 | 5,883,209.54 | 1,851,355.59 | 76.06 |
| 6244 | 4,294,168.81 | 2,958,100.25 | 68.89 | 1,609,294.67 | 1,609,294.67 | 100.00 | 5,903,463.48 | 4,567,394.92 | 1,336,068.56 | 77.37 |
| 6251 | 915,698.51 | 818,376.50 | 89.37 | 686,947.03 | 671,857.00 | 97.80 | 1,602,645.54 | 1,490,233.50 | 112,412.04 | 92.99 |
| 6252 | 4,749,832.77 | 3,786,081.00 | 79.71 | | | | 4,749,832.77 | 3,786,081.00 | 963,751.77 | 79.71 |
| 6253 | 685,400.00 | 459,464.29 | 67.04 | | | | 685,400.00 | 459,464.29 | 225,935.71 | 67.04 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ***6254*** | 585,000.00 | 534,412.62 | 91.35 | | | | 585,000.00 | 534,412.62 | 50,587.38 | 91.35 |
| ***6255*** | 20,000.00 | 7,300.00 | 36.50 | | | | 20,000.00 | 7,300.00 | 12,700.00 | 36.50 |
| ***6256*** | 1,104,500.00 | 686,104.08 | 62.12 | 5,000.00 | 1,290.00 | 25.80 | 1,109,500.00 | 687,394.08 | 422,105.92 | 61.96 |
| ***6257*** | 6,000,000.00 | 4,989,032.96 | 83.15 | | | | 6,000,000.00 | 4,989,032.96 | 1,010,967.04 | 83.15 |
| ***6258*** | 5,018,700.00 | 4,800,763.51 | 95.66 | | | | 5,018,700.00 | 4,800,763.51 | 217,936.49 | 95.66 |
| ***6259*** | 10,331,790.00 | 9,997,896.05 | 96.77 | | | | 10,331,790.00 | 9,997,896.05 | 333,893.95 | 96.77 |
| ***6271*** | 642,050.56 | 497,405.37 | 77.47 | | | | 642,050.56 | 497,405.37 | 144,645.19 | 77.47 |
| ***6313*** | 24,650,069.85 | 13,187,994.83 | 53.50 | | | | 24,650,069.85 | 13,187,994.83 | 11,462,075.02 | 53.50 |
| ***6417*** | 53,571.43 | 19,133.33 | 35.72 | | | | 53,571.43 | 19,133.33 | 34,438.10 | 35.72 |

ካፒታል

| | የተፈቀደ/የተስተካከለ | ወጪ የተደረገ | ወጪ የተደረገ % | | | | አጠቃላይ የተፈቀደ በጀት | በአጠቃላይ ወጪ የተደረገ | ልዩነት | ወጪ የተደረገ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የበጀት አርዕስት | 262,691,211.27 | 247,356,555.25 | 94.16 | | | | 262,691,211.27 | 247,356,555.25 | 15,334,656.02 | 94.16 |
| 6115 | 13,114,605.00 | 12,748,122.36 | 97.21 | | | | 13,114,605.00 | 12,748,122.36 | 366,482.64 | 97.21 |
| 6124 | 990,128.00 | 899,590.43 | 90.86 | | | | 990,128.00 | 899,590.43 | 90,537.57 | 90.86 |
| 6322 | 183,976,399.32 | 169,918,661.01 | 92.36 | | | | 183,976,399.32 | 169,918,661.01 | 14,057,738.31 | 92.36 |
| 6323 | 62,660,078.95 | 62,660,078.95 | 100.00 | | | | 62,660,078.95 | 62,660,078.95 | - | 100.00 |
| 6324 | 0.00 | 0.00 | | | | | 0.00 | 0.00 | - | |
| 6326 | 1,950,000.00 | 1,130,102.50 | 57.95 | | | | 1,950,000.00 | 1,130,102.50 | 819,897.50 | 57.95 |
| □/□ምር | 518,558,630.30 | 472,399,868.26 | 91.10 | 38,037,894.67 | 36,303,053.38 | 98.51 | 556,596,524.97 | 508,702,921.64 | 47,893,603.33 | 91.40 |

ያዘጋጀው፡ ---------------------------------------- ያረጋገጠው ፡ ---------------------------------------- ያፀደቀው፡ ----------------------------------------

**ማስታወሻ**

በ 2012 በጀት ዓመት ከላይ እንደታየው የፋይናንስ አጠቃቀሙ **91.40 %** ሲሆን ነገር ግን በዚሁ በጀት ዓመት በአድቫንስ ክፍያ ተከፍሎ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ያልተወራረደ ብር **25,968,011.43** ( ሃያ አምስት ሚሊየን ዘጠኝ መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አስራ አንድ ከ አርባ ሶስት ሳንቲም ) ያለ በቅድመ ክፍያ ተከፍለው ያልተወራረዱት ክፍያዎች ዝርዝር

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ኤስ ኤ ኮንስትራክሽን | 4,978,366.21 |
| 2 | ባንቲዋሉ ኮንስትራክሽን | 14,496,132.52 |
| 3 | የፒኤች ዲ ተማሪዎች ክፍያ | 1,485,000.00 |
| 4 | የሪሰርች ክፍያ | 811,146.58 |
| 5 | ሳስኮ ኢንዱስትሪያል ትሬድ | 4,197,366.12 |
| | ***ድምር*** | ***25,968,011.43*** |

## International and Public Relations Coordination Directorate


**Contact Address:**

Tel.0116 46 2887,Extension: 253/252/257 , Fax: 0116463016

P.O.Box5648, E-mail: www.Iprd @ecsu.edu.et ,

Website: www.ecsu.edu.et, Tweeter: @ECSU tweets ,FM Radio:-100.5MHz

Facebook: Ethiopian Civil Service University





BUILDING CAPACITIES IN PUBLIC SECTOR SINCE 1995


**PRINTED BY** *International & Public Relations Directorate*